# ሕዝብ ጥቅሙን እንዲቃወም የተካሄደ ዘመቻ

አዲስ ቶልቻ

የከተማ ቦታን በሊዝ ስለሚይዝ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ፀደቀ ሕዳር 18/2004 ዓ/ም በነጋሪት ጋዜጣ የወጣው አዋጅ የሠሞኑ የመወያያ አጀንዳ ለመሆን በቅቷል፡፡ የዚህን አዋጅ ማሰረታዊ ይዘት ለሚረዳት ከአዋጁ ከማኅት ይልቅ የአፌደሪ ሕገመንግሥት ላይ ስለሜሬት ይዞታና አጠቃቀም የተደነገገወን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

የአፌደሪ ሕገመንግሥት አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 "የገጠርም ሆነ የከተማ ሜሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ ሜሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው" ይላል፡፡ ባለሃብቶች በዚህ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት በሆነ ሜሬት የሚጠቀሙበትም ሁኔታ በዚሁ አንቅፅ ንኡስ አንቀጽ 6 ላይ "መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በሜሬት የመጠቀም መብታቸወን ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሠናል" በሚል ሰፍሯል፡፡

"የከተማ ቦታን በሊዝ ስለማያዝ" በሚል በቅርቡ የወጣው አዋጅ፣ በዋነኛነት ከላይ በተጠቀሱት የሕጎች ሁሉ ምንጭ የሆነው ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአዋጁ ላይ አስተያየት የሰጡ አንዳንድ ግለሰቦችና የፖሎቲካ ፓርቲዎች፣ የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅ ላይ ያሉትን ድንጋጌዎች፣ ከዚህ ቀደም የሚይታወቅና አዲስ አድርገው ያቀረቡበትን ሁኔታ አስተወለናል፡፡ በተለይ አነጋጋሪ የሆነው የአዋጁ ክፍል ነባር ይዞታን የሚመለከተው ነበር፡፡ አዋጁ "ነባር ይዞታዎችን ወደ ሊዝ ስሪት ስለሚቀየርበት ሁኔታ" በሚለው ርዕስ ንዑስ (አንቀፅ 6) ስር ይህን ጉዳይ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በግልፅ አስፈሯል፡፡ በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 በነባር ይዞታ ላይ የሠፈረ ንብረት ባለቤትነት ከወርስ በስተቀር በማንኛወም መንገድ ለሌላ ሰው ሲተላለፍ፣ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው የቦታው ባለይዞታ ሊሆን የሚችለው በሊዝ ሥሪት መሠረት ይሆናል" ይላል፡፡ ከዚህ ባለፈ፣ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለማያዝ የወጣው አዋጅ ከዚህ፣ "ነባር ይዞታዎች በቀጥታ ወደሊዝ ይተላለፋሉ" የሚል ድንጋጌ የለወም፡፡ ነባር ይዞታ ወደሊዝ ሥርዓት የሚገባው፣ ባለይዞታው በሜሬቱ ላይ ያለወን የመጠቀም መብት በቃኝ ብሎ ሜሬቱን ከወርስ ወጭ ወደሌላ ወገን ሲያስተላልፍ ብቻ ነው፡፡ በወርስ ሲዘዋወር ነባር ባለይዞታነቱ እንደነበረ ይቀጥላል፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ በሕዝቡ ዘንድ የተነሳና ጎልቶ የወጣ አንድ ጥያቄ ተስተውሏል፡፡ይህም አዋጁ ነባር ባለይዞታዎች "የእኔ ነው" ብለው ይዘወት የቆዩትን ሜሬት በሽያጭ ወደ ሌላ ሰው አዘዋወረው የመጠቀም መብታቸወን ያሳጣል የሚለው ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ግልፅ እይታ ይኖረን ዘንድ ቀደም ሲል ከጠቀስነው የሕገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 አኳያ ማየት ይኖርብናል፡፡ በዚሁ የሕገመንግስቱ አንቀፅ መሠረት ሜሬት የግለሰቦች የግል ሃብት አይደለም፤ የሕዝብና የመንግሥት የጋራ ሐብት እንጂ፡፡ በመሆኑም በቅርቡ ከወጣው የሊዝ አዋጅ ቀደም ሲል ሜሬት የያዙ

ግለሰቦችም በመሬቱ ላይ ያላቸው መብት የመጠቀም መብት ብቻ ነበር፡፡ መሬቱን የያዙት ከመንግስት ጋር በገቡት የኪራይ ውል በመሆኑ የኪራይ ይዞታ መሆኑ ማታወቅ አለበት፡፡ ባለይዞታዎች የቦታ ግብር በሚል መሬቱ እንደሚገኝበት ከተማ በካሬ ሜትር የተወሰነ የኪራይ ክፍያ በየአመቱ ሲከፍሉ መቆየታቸውም ይታወቃል፡፡ ለማለት የተፈለገው ይህ አሁን የወጣው የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅ የነባር ባለይዞታዎችን የኪራይ ባለይዞታነት መብት አልነካም፡፡ ይሁን እንጂ ነባር ባለይዞታው በኪራይ የያዘው መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት "በቃኝ" ብሎ ከወርስ ውጭ ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን ሲያዘዋውር፣ አዲሱ ባለይዞታ መሬቱን የሚይዘው ከመንግስት ጋር በሚገባው የሊዝ ስምምነት ይሆናል፡፡ የከተማን መሬት አጠቃቀምና ባለይዞታነት የሚወስን አዋጅ ወጥቶ በስራ ላይ በመዋሉ አዲሱ ባለይዞታ በዚህ አዋጅ መሠረት ከመንግስት ጋር የሊዝ ውል ተስማምቶ መሬቱን እንዲይዝ ይደረጋል ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ በብዙዎች ዘንድ መደናገርን የፈጠረው፣ "ነባሩ ባለይዞታ በመሬቱ ላይ የነበረውን የመጠቀም መብቱን ለሦስተኛ ወገን አሣልፎ ሲሰጥ የሚያገኘው ጥቅም ምንድነው?" የሚለው ነው፡፡ ይህ መደናገር የተፈጠረው መሬትን ሕገመንግስቱ ላይ ከሰፈረው ድንጋጌ ውጭ እንደሚሸጥና እንደሚለወጥ የግል ንብረት በመመልከት ነው፡፡ ይህም "ባለይዞታው መሬቱን የመሸጥ መብት ነበረው፣ አዋጁ ይሕን መብቱን ነጠቀው" የሚል የተሳሳተ ማሳሻ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ግለሰቦች ወትሮም የባለቤትነት መብት ያላቸው በመሬቱ ላይ ሳይሆን፣ በመሬቱ ላይ ባፈሩት ንብረት ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህም ሆኖ፣ ማለትም ነባር ባለይዞታዎች የባለቤትነት መብቱ የሕዝብና የመንግስት በሆነው መሬት የመጠቀም መብት ስላላቸው፣ ይህን የመጠቀም መብታቸውን አሳልፈው ማስጠት ይችላሉ፡፡ እዚህ ላይ ሚጩው የሚሬቱ ባለይዞታ መሬቱን የሚይዘው ከመንግስት ጋር በበሚገባው የሊዝ ስምምነት ማሰረት ነው ካልን፣ ይህ መሬቱን የመጠቀም መብቱን አሳልፎ የሚሰጠው ነባሩ ባለይዞታ ወደሚያገኘው ጥቅም እንመለስ፡፡

በቅረቡ የወጣው የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅ የነባር ይዞታን የመጠቀም መብትን የማስተላለፍ ጥያቄን በተመለከተ ግልፅ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 7 "ወደ ሊዝ ሥሪት የሚገቡ ይዞታዎችን በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆነው የሊዝ ክፍያ ማጠን በአካባቢው የሊዝ ማነሻ ዋጋ መሠረት ይሆናል" ይላል፡፡ እዚህ ላይ በሊዝ ማነሻ ዋጋና በጨረታ የሊዝ ዋጋ መሃከል ሠፊ ልዩነት ያለ መሆኑ ሊታወስ ይገባል፡፡ ለምሣሌ አዲስ አበባ ላይ እስካሁን የሚሰራበት የሊዝ የመነሻ ዋጋ በካሬ ሜትር 200 ብር ነው፡፡ ይሁን እንጂ መሬቱ እንደሚገኝበት ሁኔታ በካሬ ሜትር ከ 20 ሺህ ብር በላይ የሊዝ ጨረታ ዋጋ የተሸጠበት ሁኔታም ተስተውሏል፡፡ በሊዝ የመነሻና የጨረታ ዋጋ መሃከል ያለው ልዩነት ይህን ይመስላል፡፡

እንግዲህ አንድ ነባር ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ያለውን የመጠቀም መብት ለሌላ ግለሰብ /ድርጅት/ አሣልፎ ሲሰጥ፣ መንግስት ከአዲሱ ባለይዞታ ጋር የሊዝ ሥምምነት የሚገባው በጨረታ ሣይሆን በሊዝ ማነሻ ዋጋ ነው ማለት ነው፡፡ ነባር ባለይዞታውና አዲሱ ባለይዞታ በመነሻና በጨረታ ዋጋ መሃከል ባለው ልዩነት ላይ ይደራደራሉ፡፡ በሁለቱ ስምምነት ማሰረት ከሊዝ ማነሻ ዋጋ በላይ ያለውን ክፍያ የሚያገኘው ነባር ባለይዞታው ይሆናል፡፡ እርግጥ በሊዝ

ማሻሻና በጨረታ ዋጋ ማሃከል ነባር ባለይዞታወን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል ጉልህ ልዩነት እንዲኖር ሜቱ በአግባቡ የለማ ሊሆን ይገባል፡፡ ሜቱ በሚገኝበት አካባቢ የማስረተ ልማትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴም በዋጋው ልዩነት ላይ ተፅእኖ አለው፡፡ የሜት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛንም እንዲሁ ትፅእኖ ይኖረዋል፡፡ መንግስት ለሊዝ የሚያቀርበው ሜት፣ ማለትም የሜት አቅርቦት ማጠን ከፍላጎት ጋር ያለው ንፅፅር በጨረታ መድረሻ ዋጋ ላይ እንዲሁ ተፅእኖ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ ዋናው ትኩረት ሊሠጠው የተፈለገው ነባር ባለይዞታው የማጠቀም መቡቱን ለሦስተኛ ወገን ሲያሣልፍ ከጨረታ ማሻሻ በላይ ባለ ዋጋ ላይ የሚደራደር መብት ያለው መሆኑና፣ የሚያገኘው ጥቅምም ከሊዝ ማሻሻ ዋጋ ባላይ ያለው በሜት የማጠቀም መቡቱን ተደራድሮ ያስተላለፈበት ዋጋ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር መንግስት ከአዲሱ ባለይዞታ ጋር የሊዝ ወል ከሚገባበት ማሻሻ ዋጋ በላይ ያለው የሜት ዋጋ ለነባር ባለይዞታው የሚከፈል ነው፡፡

ነባር ይዞታን ከማዘዋወር ጋር በተያያዘ አዋጁ የሚለው ከላይ የተጠቀሱት ቢሆንም፣ አዋጁ የመጣባቸውና ድንጋጤ ላይ የወደቁ ወገኖች እንዳሉ ግን ይታወቃል፡፡ እነዚህ ወገኖች ሜት ከያዙ በኋላ፣ ካፒታላቸውን ኢንቨስት አድርገው ከማልማት ይልቅ አጥረው በማቆየት በከፍተኛ ዋጋ እየሸጡ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሲያጋብሱ የቆዩ ናቸው፡፡ የዚህ አይነት ግለሰቦች በከተሞች አካባቢ ካፒታላቸውን፣ እወቀታቸውንና ጉልበታቸውን ኢንቨስት አድርገው ትርፍ የሚያስገኝ አንድም የልማት ሥራ ሣይሠሩ ንብረትነቱ የሕዝብና የመንግስት የሆነን ሜት በማቀባበል ብቻ በአጭር ጊዜ ወስጥ "ከሠማይ ወረደላቸው እንዴ!" እስከሚያስብል ድረስ ሚሊየነር ለመሆን በቅተዋል፡፡

አሁን የከተማ ቦታን በሊዝ ስለማያዝ የወጣው አዋጅ ይህን ሕገወጥና ተገቢ ያለሆነ ከፍተኛ ጥቅም ያስቀራል፡፡ በአዋጁ ላይ ከፍተኛ ተቃወሞ ያቀረቡትም እነዚህ ሕገወጥ ጥቅም የቀረባቸው ጥቂት ግለሰቦች ናቸው፡፡

እነዚህ አዋጁ የመጣባቸው ግለሰቦች አደናግረው ከጎናቸው የሚሰለፉ ዜጎችን ለማፍራት ካነሱዋቸው ሚደናገሪያዎች ማሃከል፣ "አዋጁ ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል ሜት የሚያገኝበትን ዕድል ይዘጋል፡፡ የሚጠቅመው ገንዘብ ላላቸው ባሐብቶች ብቻ ነው" የሚለው ይገኝበታል፡፡ እነዚሁ ግለሰቦች እንደግለሰብም እንደዜጋም ከአዋጁ ተጠቃሚ የሚሆኑ ዜጎችን አደናግረው ለተቃወሞ አብረዋቸው እንዲሠለፉ ለሚድረግም ጥረዋል፡፡ ሕዝቡ ወስጥ ለተፈጠረው ሚደናገር ዕወነታውን አዛብተው ያቀረቡ የተወሰኑ የማናኛ ብዙሃን አስተዋፅኦም አለበት፡፡

መንግስት ያወጣው የሊዝ አዋጅ አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸወን የከተማ ነዋሪዎች ባለመኖሪያ ቤት ለማድረግ የተያዘወን ፖሊሲ አይፃረርም፡፡ የጋራ የተፈጥሮ ሃብት ከሆነው ሜት ላይ መንግስት የሚያገኘወን ገቢ በማስደግ ማስረተ ልማት ልማቶችን ማሟላትና ማስፋፋት የሚያስችል አቅም ይኖረዋል፡፡ መሠረተ ልማት በተሟላላቸው አካባቢዎች የኮነዶሚኒየም ቤቶችን የማስገንባት አቅሙን ያሳድጋል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ ገቢ ያላቸወን ዜጎች የመኖሪያ ቤት

ባለቤት ማድረግ ላይ ላተኮረው ለሪል ስቴት ግንባታ መሰረተ ልማት የተሟላለት የመሬት አቅርቦት ለመፍጠር የሚያግዝ ነው፡፡

በግል የመኖሪያ ቤት ለማንባት ለሚፈልጉ ዜጎችም መሬት በዉድድር የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች ይጎዳል የሚባለው ለሊዝ የሚከፍሉትን ዋጋን በማሰብ ከሆነ፣ አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ያተኮረው የኮንዶሚኒየም የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ እነደተጠበቀ ሆኖ፣ መኖሪያ ቤት ለማንባት በሊዝ መሬት የሚወስዱት ሰዎች የሊዝ ክፍያውን የሚፈፅሙት በአንድ ጊዜ ሳይሆን በ50 ዓመት በመሆኑ ክፍያው ከአቅም በላይ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አሁን የከተማ መሬት ግብር እየተባለ ነባር ባለይዞታዎች ከሚከፍሉት ኪራይ የበለጠ አለመሆኑም መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ከምንም በላይ መታወቅ ያለበት ግን መሬት የሕዝብ የጋራ ሐብት የሆነና ዋጋ ያለው የምርት ግብአት በመሆኑ፣ መንግስት ከመሬት የሚያገኘውን ገቢ በማሳደግ በአጠቃላይ ለዜጎች ሊያስገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ነው፡፡

አዋጁ መሬትን እንደ ግብአት በመጠቀም ሐብት ማፍራት ለሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች መሬት ለማግኘት በሚከፍሉት የሊዝ ክፍያ የሚገኘው ገቢ የከተማን መሠረተ ልማት ለማስፋፋትና ለማንባት ይውላል፡፡ ዜጎች የተሟላ የመንገድ፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ... አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስቻል የመንግስትን አቅም ያጎለብታል፡፡ በዚህ አኳኋን ባለሐብቶችም ይሁኑ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን ማግኘት ይችላሉ፡፡ በሕገመንግስቱ መሰረት የሕዝብ የጋራ ሃብት ከሆነው መሬት፣ ሕዝብ ተጠቃሚ መሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

አዋጁ ከባለሐብቶች፣ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ዜጎችና በአጠቃላይ ከሕዝብ ጋር በተያያዘ በተገናኘ የሚኖረውን ፋይዳ በዝርዝር ማቅረብ ሌሎች አዋጆችን ደንቦችንና ፖሊሲዎችን መጥቀስ ስለሚፈልግ ለማጠነኛ ዕይታ ይህን ያህል ካልኩ ይብቃኝ፡፡ አሁን በአዋጁ ላይ የተወሰኑ ፖለቲከኞች ወደያዙት አቋም ልማለስ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) አዋጁን በተመለከተ ከወራት በፊት መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡ **ባለፈው ሐሙስ ጥር 17ም በዚሁ ጉዳይ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ መግለጫ አውጥቷል፡፡ የሁለቱ መግለጫዎች ይዘት ተመሣሣይ በመሆኑ በሁለቱም ላይ የተነሱት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አተኩራለሁ፡፡** መድረክ በአዋጁ ላይ ባወጣው መግለጫ "የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጁ የከተማ ነዋሪዎችን ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የማስተላለፍ መብት የሚሸረሽር ነው፤ አዋጁ በተዘዋዋሪ የዜጎች ሃብት ነጠቃ ነው፤ የከተማ ነዋሪ ዜጎችን ሕገመንግሥትዊ መብት ገፎም የመንግስት ጭሰኛ ያደርጋል፤ ሕገመንግሥቱ ለሕዝቡ ያረጋገጠውን የንብረት ባለቤትነት መብት /ቤትና ከቤት ጋር የተያያዘ መሬትን ጨምሮ/ ያይፃረራል" ይላል፡፡ ይሄው የመድረክ መግለጫ በማጠቃለያው "በገጠር ነዋሪው አርሶ አደር የይዞታው ባለቤት መሆን እንዳለበት ሁሉ የከተማ ነዋሪወም የመኖሪያ ቤት የሠራበት መሬት ባለቤትነት

እንዲረጋገጥ ትግሉን እቀጥላለሁ” ይልና ፣ በሜጨሻም ለዚህ ትግሉ ሕዝቡ ከጎኑ እንዲሰለፍ ጥሪ አቅርቧል፡፡ እስቲ እነዚህን የሙድረክ አቋሞች አንድ በአንድ እንሜልከት፡፡

ሙድረክ “አዋጁ የከተማ ነዋሪዎችን ንብረት የሜፍራት፣ የሜስተዳደርና የሜስተላለፍ መብትን ይነጥቃል፡፡ ይህም የዜጎችን ሕገመንግሥታዊ መብት ይሸረሽራል” ብሏል፡፡ ይህን የሙድረክ አቋም ለሚዳት በቅድሚያ የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ላይ ስለንብረት ባለቤትነት የተደነገገወን መሜልከት ጠቃሚ ነው፡፡ ሕገመንግስቱ በአንቀፅ 40 ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ “ማንኛወም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት ሙሆኑ/ሙሆኗ ይከበርለታል/ይከበርላታል፡፡ ይህ ሙብት የሕዝብን ጥቅም ለማጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የሜያዝና በንብረት የማጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች ሙብቶች እስካልታቃረነ ድረስ ንብረትን የሜሸጥ፣ የሜውረስ ወይም በሌላ ማንግድ የሜስተላለፍ ሙብቶችን ያካትታል” ይላል፡፡

በዚሁ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 2 ስለግል ንብረት ምንነት ሲገልጽም፣ “ማንኛወም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰወነት በሕግ የተሰጣቸው የኢትዮጵያ ማህበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንደሆኑ የተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በሜፍጠር ችሎታቸው፣ ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሣይኖረው ዋጋ ያለው ወጤት ነው” ይላል፡፡ ሕገመንግስቱ ከላይ ከተጠቀሰወና ለንብረት ምንነት ከሰጠው ትርጉም አኳያ በቅርቡ የወጣው የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅ፣ በሕገመንግስቱ የተደነገገወን ንብረት የሜፍራት ሙብት አይፃረርም፡፡

ሜሬት የተፈጥሮ ሃብት ሲሆን ጉልበትን፣ የፈጠራ ችሎታን ወይም ካፒታልን በማጠቀም ሀብት ሜፍራት የሜያስችል ማሰረታዊ ግብዐት ነው፡፡ ሜሬት በራሡ እንደግል ንብረት የሜቆጠር ሀብት ሣይሆን፣ ሀብት ሜፍጠር የሜያስችል ግብአት ነው፡፡ በሙሆኑም እንደግል ንብረት ሊታይ የሜቻልበት የሜርህ አግባብ የለም፡፡ ሰዎች በሜሬቱ ላይ ያፈሩት ሐብት ግን እንደ ግል ንብረታቸው ይቆጠራል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ሁሉም ዜጎች በተፈጠሩበትና የዜግነት ሙብት ባላቸው አገራቸው ላይ በጋራ የሜሬት ባለቤትነት ሙብት አላቸው ሲል የደነገገወም፣ ሜሬትን ማንም ጠፍጥፎ ያልሰራው በሙሆኑና ሰዎች ምድር ላይ በሜፈጠራቸው ማንም ሊከለክላቸው የሜይችለው የማጠቀም ሙብት ያላቸው የተፈጥሮ ሃብት ሙሆኑን ማሳሻ በሜድረግ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ሜሬት ንብረት ለሜፍራት አስፈላጊ የሆነ ሙሠረታዊ ግብአት በሙሆኑ በአንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 6 ላይ “ማንግስት ለግል ባለሐብትና በሕግ በሜወሰን ክፍያ በሜሬት የማጠቀም ሙብታቸወን ያስከብርላቸዋል” ይላል፡፡ አፈፃፀሙ በሕግ እንደሜወሰንም ይገልፃል፡፡ (በቅርቡ የፀደቀው የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ አፈፃፀማን ለመወሰን የወጣ ህግ ነው፡፡) እንግዲህ አዋጁ በሕገማንግስቱ ላይ የሰፈረወን የዜጎችን ሀብት የሜፍራት ሕገመንግሥታዊ ሙብት የሜፃረረው በምን አኳኋን ይሆን? ይህን ጥያቄ ለሙድረኮች ሙተው ይቀላል፡፡

የከተማ ቦታን በሊዝ የማያዝ አዋጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዜጎች ሀብት ነጠቃ መሆኑንም መድረክ በመግለጫው ላይ ጠቅሷል፡፡ በዚህ ዙሪያ ሕገመንግስቱ የሚለውን ከመጥቀሳችን በፊት፣ ከሀብት/ንብረት ጋር በተያያዘ የሊዝ አዋጁ ላይ የሰፈረውን ለግንዛቤ ይሆነን ዘንድ እንመልከት፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ግንኙነት ያለው ሆኖ ያገኘሁት የአዋጁን ክፍል 4 "የከተማን ቦታ ስለማስለቀቅ" የሚለው ድንጋጌ ነው፡፡ በዚህ የአዋጅ ክፍል (አንቀፅ 25 ንኡስ አንቀጽ 1) ስር፣ "ቦታ በሊዝ ወስዶ በሕጉ መሠረት ጥቅም ላይ ያልዋለ፣ ቦታው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ አገልግሎት ሲወሰን ወይም የሊዝ ይዞታ ዘመኑ ሲያበቃ፣ ከቦታው ላይ ለሚነሳው ንብረት/ሃብት በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሣ ይከፈላል፣ ምትክ ቦታም ይሰጠዋል፡፡" ይላል፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው መሬት ለሕዝብ ፋይዳ ያለውን ልማት ለማከናወን የሚያስችል ማስረታዊ ግብአት ነው፡፡ አንድ ግለሰብ መሬት በሊዝ ሲይዝ ዋና አላማው በመሬቱ ማጠቀም ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ መሬት ጌጥ አየደለም፡፡ እናም ግለሰቡ መሬቱን ካላለማው፣ ከመሬቱ ሊገኝ ይችል የነበረውን ጥቅም በማስቀረቱ መሬቱ ተነጥቆ ለሌላ ሚልማት ለሚችል ሰው ማስጠት አለበት፡፡ እንግዲህ ይህ የሊዝ አሰራር ሰዎች በጉልበታቸው፣ በመፍጠር ችሎታቸው፣ በካፒታላቸው ያፈሩትን ሀብት ወይም ንብረት መውረስ የሚሆነው በምን አኳኋን ነው?

"አዋጁ የከተማ ነዋሪውን ሕገመንግስታዊ መብት ገፍፎ የመንግስት ጢሰኛ ያደርጋል" ብሏል፣ መድረክ በመግለጫው፡፡ ይህን የመድረክ የተቃውሞ ሃሳብ ለመረዳት በቅድሚያ የጢሰኛን ምንነት እንመልከት፡፡ ጢሰኛ ማለት በግለሰብ ርስትነት የተያዘ መሬት ላይ የግለሰቡን መሬት እያለማ ምርቱን ለባለሬቱ እየገበረ መሬቱ ላይ የሚኖርበት ጥግ ብቻ ስለተሰጠው ጉልበቱንም ጭምር እየገበረ የሚኖር ሰው ነው፡፡ ጢሰኛ መሬቱን በርስትነት ለዘለአለም የማያዝ፣ የማሻጥና የማለወጥ መብት የሌለው ማለት ሣይሆን፣ በመሬቱ ላይ በጉልበቱና በዕወቀቱ የሚያመርተው ምርት ላይ የባለቤትነት መብት የሌለው፣ የራሱም ጉልበት ላይ ሙሉ በሙሉ የማዘዝ መብት የተነፈገውና የገዛ ምርቱን ባለቤትነት ያጣ አርሶ አደር ማለት ነው፡፡ እናም መሬትን በሊዝ በማያዝ ሀብት/ንብርት የማፍራት መብትን የሚፈቅደው አዋጅ በምን አኳኋን ነው ባለሊዙን ጢሰኛ የሚያደርገው? መድረኮችም ሆኑ ሌሎች ይህን ቢያስበቡት ሚልካም ይማስለኛል።

በተለይ ሠሞኑን ባወጣው መግለጫ ላይ የሊዝ አዋጁ ለሕዝብ ድምፅ ወሳኔ መቅረብ አለበት የሚል አቋም ይዟል፡፡

ድምፀ ውሣኔን በተማለከተ አንድ ማታወቅ ያለበት ነገር ሕገመንግስቱ ላይ በግልፅ የተቀማጠ መሆኑ ነው፡፡ የትኛው ጉዳይ ለሕዝብ ወሳኔ እንደሚለክ ሕገመንግስቱ ይገልፃል፡፡ ሕገመንግስቱ ላይ ስለመሬት ባለይዞታነት የወጣውን ድንጋጌ ማስፈፀም የሚያስችሉ አዋጆችን ማውጣት አዋጅ የማውጣት ሕገመንግስታዊ ሥልጣን ያለው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው፡፡ ይህ የሕዝብን የተማከለ ከፍተኛው የመንግስት የሥልጣን ባለቤት ሕገመንግስቱንና የሕዝቡን ጥቅም የሚፃረር ወሳኔ አያፀድቅም፡፡ ሕዝብ ማንዘብ ያለበት በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ሕዝብ ማክሮ ዘክሮ ድምፅ እየሰጠ

የሚሄደበት አሠራር ወስብስብና በተጨባጭ ምንም የማያራምድ በመሆኑ፣ ሕዝብ ይህን የሚያደረግ ሥልጣኑን በወኪልና ለፓርላማ እንዲሰጥ የሚደረግበት የዴሞክራሲ አሠራር ማዘርጋቱን ነው፡፡

ከዚህ የተሻለ በተጨባጭ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ የአሠራር ሥርዓት የለም፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅን ያወጣው ሕገመንግስቱን ለማስፈፀም በሕዝብ ወኪልና የተሰጠው አዋጅ የማውጣት ሥልጣኑን ተጠቅሞ ነው፡፡

የመድረክ አመራሮች የሊዝ አዋጁን በተመለከተ ሕዝብ ድምፅ ይስጥበት ሲሉ ከላይ ከተገለፀው ሕገመንግስታዊና ዴሞክራሲያዊ አሠራር አኳያ ማየትን አልመረጡም፡፡ ም/ቤቱ በመሬት ጉዳይ ላይ አዋጅ የማውጣት ሕገመንግስታዊ መብት አለው ወይንስ የለውም የሚለውንም ጉዳይ ማንሣት አልወደዱም፡፡

በደፈናው ሕዝብ ድምፅ ይሰጥበት ያሉት እስካሁን ከተወሰኑ ጥቅማቸው ከተነካባቸው ማናኛ ብዙሃን ጋር ሕዝቡ ወስጥ ለፈጥ ለፈጥሩት ያሰቡት ወዥንብር ሥር ይዞ ከሆነ በግርግር ከረር ያለ ሁከት ቀመስ ተቃውሞ ለማስነሣት ያስችላል ከሚል ግምት ተነስተው መሆኑን የከዚህ ቀደም ባሕሪያቸውን ለሚያወቅ የተሰወረ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ፣ በቅርብ የወጣው የከተማ ቦታ የሊዝ አዋጅ ላይ የቀረበው ተቃውሞ ዋነኛ መነሻ የሕዝብ ሃብት ከሆነው መሬት ሲያጋብሱ የቆዩትን ሕግ ወጥ ጥቅም ያስቀረባቸው ደላሎች ናቸው፡፡ ከየትም የመነጨ ተቃውሞን ከህዝቡ ጥቅምና ፍላጎት፣ ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ለመመርመር ፋታ ሳይወስዱ ለተቃውሞ ፖሎቲካ ፍጆታነት በማዋል አመላቸው የሚታወቁ የተወሰኑ ፖለቲከኞችም ሕገወጥ የመሬት ደላሎችን ወሬ በማራገብ ተባባሪነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ ሁለቱም ሕዝብ ተደናግሮ የራሱን ጥቅም እንዲቃወም ለማነሳሳት መሞከራቸው መታወቅ ይኖርበታል፡፡